Be careful in partnership deeds, spousal relations, mental worries and confusion. Guard against depression and feeling low, it is only in the mind, it is illusory. Domestic problems may occur, so keep a low profile; your arguments will only lead to more problems. Expenses may be more than the income. Younger siblings may be having a tough time on domestic and professional front. Health issues may occur from indigestion, skin rashes to stomach ailments. Journalists, media people, Govt. job seekers, stand to gain. Luck days: All except Saturday.

(Watery sign, ruling planet is Moon) - (June 22 – July 22)

## LEO



You will remain happy despite of many obstacles. Your personal and Professional front both seem to be comfortable, but you may still feel a void within you. Attend to your children; they may need medical and academic attention. Domestic happiness prevails despite of much strife and problems at home; spend more time with family. Do not gamble; spend money wisely as your expenses will be on the higher side. Health wise; you may get skin rashes or may face cough, cold or indigestion, so take care. Luck days: Sun, Wed, Thu & Friday.

(Fire sign, ruling planet is Sun) - (July 23 – August 22)

## VIRGO



Your keen interest in mystic and esoteric sciences will surprise you. You will gain through your children tremendously, Matrimonial and business alliances will be fruitful. Happy domestic conditions prevail. Financially, some may loose money if the venture is not planned properly; otherwise you will be quite happy as all your commercial ventures will meet with success. Professionals in communication business, teachers, and mathematicians will stand to gain professionally. Some people may complain about Liver, stomach related problems, moderation in eating is advised. Luck days: Thu, Fri & Saturday.

(Earthen sign, ruling planet is Mercury) (August 23 – Sept. 22)

## LIBRA



You will have great interest in Music, Art and Romance, all your artistic and creative talent will meet with success. You will steal the show wherever you go. There is social recognition and up-liftment in your circle. Keep away from any extra marital affairs. Money, finance, domestic happiness and peaceful conditions prevail all around. Health is great and you are confident of your actions. Try a few outings, picnics, social gatherings; they will give you joy and happiness. Luck days: Sun, Wed, Thu & Friday.

(Air sign, ruling planet is Venus) - (September 23 – October 23)


## SCORPIO



You are bold and courageous, spiritual and pious. Your mind will be clouded with thoughts of eternal happiness, Nirvana and fulfillment. Too much thinking to lead to confused state of mind. Business and Matrimonial alliances will mature and meet with success. Despite of your hard work you may not be rewarded in same proportion; good times are ahead, you are sowing the seeds of success, so be happy and content. Your domestic conditions are happy and cordial. Just be extra careful in your judgement of situations. Luck days: Sun, Wed, Thu & Friday.

(Water sign, ruling planet is Mars) - (October 24 – Nov 22)

## SAGITTARIUS



Beware of using harsh words in your speech; this may lead to further troubles. The more spiritual you are at this point in time, it is better for you. Domestic and financial conditions may not be the best. Your expenses will be higher than income. Spend more time with family, be closely bonded with them, take care of their health, moderation in eating and drinking is advised. Spend more time with the children; they need your support at the moment. Guard against cheating, gambling, speculation or theft; don't drink and drive. Count less on luck and do more efforts in every respect. Luck days: Sun, Wed, Thu, Fri & Sat.

(Fire sign, ruling planet is Jupiter) - (Nov 23 – Dec 21)

## CAPRICORN



You will feel happy, energetic and full of life despite of many obstacles. Domestic troubles are seen for some due to economic and financial constraints. Marriage and Business alliances may not work; marital separation is seen for some. Positive outlook will change depressed situations and will boost your energies tremendously. Communicate well, "understand to be understood". Be spiritually inclined and spend more time in spiritual and religious practices, it will give you great joy and happiness. Your own efforts will make this month a happy one, so work on it. Some may gain through younger siblings. Luck days: Sun, Wed & Friday.

(Earthen sign, ruling planet is Saturn) - (Dec 22 – Jan 20)

## AQUARIUS



Domestic and Professional set up look fine; there is peace and prosperity at home and at work. You will enjoy a great Love life. Domestic peace and happiness prevails, it is a good time to take your partner for a vacation; Romance, passion and desires are in your mind, so make best use of this romantic mood. Finances at this time are not a constraint. Happy conditions prevail all around you. Singles should be hopeful of finding a loveable companion this week. Matrimonial and Business alliances will meet with success. Luck days: All days.

(Air sign, ruling planet is Saturn) – (Jan 21 – Feb 19)

## PISCES



You are running a great time period; happy conditions prevail at all fronts, with minor obstacles though. Things may not materialize in the same speed as per your expectations, but will materialize. You feel energetic, positive and remain charming as ever. Spousal relations may not be the best though, take the lead and correct them, seeing your determination to correct things they will listen. Money and finances are great; all your business ventures will meet with success. Health-wise you will feel great. You will be the dominant force this week, be happy and spread happiness all around you. Luck days: All days.

Water sign, ruling planet is Jupiter) - (Feb 20 to March 20)




Local(Canada) .................. $35.00
USA .............................. $45.00
Others ........................... $65.00
Institution....................... $100.00

To Place an ad, please call 416- 459-5964

or email us at: Hawarya.publications@sympatico.ca

# HISTORY MADE IN A TORONTO COFFEE SHOP - TWICE?!

*Continued from p(1)*

**By Wei Lem**

2010 Toronto --History is being made now already. Within decades, ethnic minorities shall become majorities in major cities of Canada and the entire U.S. Companies are seeking consumers; politicians and political parties seeking voters are racing to outreach to these emerging, dynamic ethnic communities.

As to history-making in a coffee shop? Firstly, on March 25, 2010, in Toronto, Canada's largest city, city Councillor Rob Ford, made history, announcing his candidacy, "I am running for Mayor." History-making, because this is the first Mayoralty candidate in recent Toronto history who has ever been labelled both as a "serious contender" by his admirers; and as a "redneck," "buffoon," and a "racist," by his critics.

Other leading candidates include Councillor George Mammoliti, former Deputy Premier, George Smitherman; former Liberal Party fundraiser Rocco Rossi; and Toronto's Deputy Mayor, Joe Pantalone. And one declared female contender, Women's Post Publisher, Sarah Thomson.

Some say Ford's announcement completes the field of serious mayoralty contenders. Is this a good sign of multiculturalism? With Councillor Ford's announcement, another Caucasian, white male joined the pack of leading contenders in the race for Mayor of Canada's largest city --a city where the visible minority population shall be the majority by 2031 (reported by official Canadian government agency, Statistics Canada, March 2010)

What are the implications of race newcomer, Councillor Ford, to Toronto's mayoralty race, and the future of Canada's largest city? What are the issues, positions of Councillor Ford and the other leading candidates vis-a-vis the various ethnic communities, the Ethiopian, pan African, and broader Toronto and Canadian society, and the world? Toronto is one of the world's most ethnically-diverse cities. In the next few months, leading up to the city election on October 25, 2010, Hawarya and I promise to dig deep for you, the readers, explore these issues, interview the candidates for Mayor and Councillors, for you, the people of Toronto.

In this month's Hawarya, we begin with Councillor Rob Ford. Why? Because, that is how I both came to meet Hawarya Publisher Muluken Muchie, and came to write this article to you. At a small, local Toronto coffee shop where Rob Ford invited a small group of media, friends and supporters, to announce to them and the world that "I am running for Mayor."




Councillor Rob Ford(front) welcoming his supporters arriving at the coffee shop, March 25/2010 at 7:00 am

First, first impressions of Publisher Muchie. Like many respected, successful community and business leaders, Mr Muchie was soft-spoken, gracious, humble as he introduced to me, the fascinating history of his community, Ethiopia Africa. Humble, as I had to delve into his wonderful personal story of success, triumph over adversity: he was a refugee from Ethiopia, who cried in despair after landing in Sudan; working hard, his efforts recognized, before subsequently being sponsored to Canada by the government of Canada and lived in Toronto, where he applied and successfully graduated from York University, and founded this paper, Hawarya, (the word means "apostle" in English) now one of Canada's largest and oldest Canadian Ethiopian, pan-African newspapers... How amazing.

What about me? I am from the Chinese Canadian community, today one of the most successful and dynamic immigrant waves to Canada; and now according to Canada's official census, the second most spoken language in Toronto, and the third most spoken in Canada. My parents immigrating to Canada in the 1950's, overcoming racism ("Chink Chinaman, go home"), meeting the many wonderful, decent Canadians; meeting each other and marrying; working hard to become successful, respected business and community leaders)! Like other stories about ethnic immigrant waves to Toronto, I found Ethiopia and Ethiopian Toronto community history both sad and inspiring! From famine in the 1980's that killed over 1 million people, to economic and government collapse in the 1990's, Ethiopian Canadians now are emerging as a new, vibrant community in Toronto, numbering over 40,000 in Metro Toronto. Seeing significant parallels to the Chinese Canadian experience in Toronto, I must admit, I warmed quickly to the candid, articulate, ever-smiling, Muluken Muchie.

By the way, this is how I came to write this article, and offered to write more political analysis on the upcoming election. While we were awaiting Rob Ford's arrival on March 25, 2010, we chatted. I told Mr Muchie that I grew up around politics and ethnic and community relations, as my family raised me to strive always to seek outreach and understanding between peoples, communities, nations. Muchie told me, he wanted that too, for his Hawarya readership and the peoples of Toronto and the world too! Another moment of history-making in that little coffee shop on Queen Street?!

Rob Ford had invited us to the coffee shop, promising a "big announcement." Something "history-making?!" Muchie and I asked together, to Ford directly, as he walked into the coffee shop, shortly after 7 a.m.

Ford smiled, offered us donuts, and swore us to secrecy, as he replied, that he was waiting for a busload of friends and supporters to arrive, and then he would be saying aloud to them, this morning, for the first time in public, and then on 640 AM radio, to the people of city of Toronto, that he was indeed running for Mayor.

So it was that in that little local Toronto coffee shop, on Queen Street, Publisher Muchie and I watched history being made. Muluken Muchie: Ethiopia African refugee; turned newspaper Publisher and respected African Canadian community member; now also witness to next chapter of Toronto history in the making! Whether or not, Rob Ford wins --especially, if Rob Ford wins-- the mayoralty race of Toronto, Toronto is forever changed. On March 25, 2010, Rob Ford, a new right-wing candidate announced, arguably, THE most right-wing candidate yet, in the race for Mayor --in a city facing ever increasing taxes and users fee; declining services; a $9.2 Billion budget, projected property tax increases of 40% over the next 4 years!

What about Rob Ford's policies? We shall examine those along with the other candidates in the days and months to come. But given Hawarya's dynamic community and readership, and the multicultural dynamism of Toronto, we wanted today, to explore the racism charges hurled against Rob Ford, the man who would be Mayor of Toronto, and one of the world's most ethnically diverse cities. A city where by 2031, the visible minority population shall become the majority. If Rob Ford fails on this issue of human respect and diversity, there should be no need to speak about him or any of his policy positions.

So while waiting for that busload of Rob Ford supporters, Mr Muchie and I had a special, quiet moment with the candidate, the man who would be king?! We put it bluntly, "what about the critics who call Rob Ford, a racist? What about his 2008 comments about "Orientals working like dogs?"

Ford laughed, his answers direct and down-to-earth, as we learned is indeed his style. Firstly, Ford said, now warming to the critic charges of racism: how many people know his family company, Deco Label, where many workers and top management are ethnic Canadians. "In fact, we are probably more multicultural than the city of Toronto," Ford said, his tone, half joke, half challenge. Secondly, Ford notes, he has coached a boys football team in Toronto, and founded a Toronto-wide football program, to assist underprivileged boys, so they can channel their energy into the joys and challenges of sport. "Where is the media on that story?" Ford laments.

And what about that publicly recorded statement that Rob Ford made in 2008: "Orientals work like dogs" that caused a media fervor, and the occupation of city hall, outside of his office?

"A false issue, created by my critics," Ford replies. "Everyone knows, this phrase is meant as a compliment, to Orientals, to anyone it is said to. This phrase has a history, a context, a meaning in this country; that we appreciate and recognize the personal and work ethos and ethics of Asian peoples, of all the decent, hard-working people of Toronto... whose hard-earned wages and taxes are being mistreated, wasted now by Mayor Miller, his supporters on Council, and other politicians, including several of my opponents in the Mayor's race. Ford was obviously thinking in mayoralty mode already!

So thankfully, the frightening racism charges against Rob Ford may be for not. We shall explore his answers against the charges of racism, and report back to you. As to Ford's public policies and their effect on the ethnic communities, all the peoples of Toronto and Canada? We shall explore these, in the coming months with you. More taxes, less taxes? More services, less services? A vision of a city and a world emerging from recession, or heading into double-dipped recession?! Stay tuned.

Ford, Smitherman, Pantalone, Rossi, Thomson. And others… By the way, the only Chinese candidate to the mayoralty race, thus far, Mr Sonny Yeung is complaining that the "mainstream media" is not giving appropriate media time to his voice and that of other minority candidates.

No doubt, history is being made in Toronto by these candidates, who would be king --who would be Mayor of one of the most ethnically diverse and well known cities in the world.

*Under the leadership of the next Mayor, Toronto shall be either a wasteland of lost opportunities and squandered tax dollars, or a future dynamic, global multicultural city of vibrant business, cultural and social opportunities to the peoples of Toronto, Canada and the world.*

# “አባቱን አክባሪ ትውልድ በሲያትል”

እ.ኤ.አ. February 13, 2010 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩን የሥነ መለኮትና የቅዳሴው ሊቅ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስን የመጨረሻ ስንብትን አስመልክቶ በተለያዩ የዜና ማሰራጫዎችና የድህረ ገፆች ላይ አይነተኛና ለምዕመናን አስደንጋጭ ዜና ሆኖ ሰንብቷል።

የብፁዕነታቸው እረፍት ያሳዘነው መላው የኢትዮጵያ ሕዝበ ክርቲያን ሆኖ ሳለ በተለይም የመንፈስ ቅዱስ ልጆቻቸውን ልብ በህዘን አቃትሎታል። ምነው እንደዚህ ሆድ ባሰህ አትበሉኝ እንጂ ሀዘኑ አንጀቴ ገብቶ አቃጥሎኛል። ምነው ? ቢባል “ኢትዮጵያ ሰው ስታጣ! ቤተ ክርስትያን ሰው ስታጣ! ምነው አልቃጠል” ወገኖቼ! ሰው ማለት እንደኔ ቆሞ ሲሔድ ሰው መስሎ የሚታየውን ማለቴ አይደለም። በሊቃውንት አባባል ሰው ማለት “ሰው በጠፋበት ዘመን ሰው ሆኖ የሚገኝ ሰው” ማለት ነው።

ታዲያ እኚህ ታላቅ አባት ሰው በጠፋበት ዘመን ሰው ሆነው የተገኙ፣ ትንሽ ትልቅ የማይሉ፣ ሰውን በሰውነቱ እንጂ በያዘው ማዕረግ (ዶክተር፣ፕሮፌሰር፣ደጃዝማች፣ግራዝማች፣ጀኔራል፣ኮሎኔል ወዘተ...) ወይም ባለው ሀብትና ገንዘብ መጠን የግለሰቡን ከሰው የበለጠ ክብርን ከምንም የማይቆጥሩ አባት ነበሩ።

ብፁዕ አባታችን በአንፃሩ በክርስትና ሕይወቱ ቀጥ ብሎ ለመራመድ አስቦ እንዳይንገዳገድ ማጥበቂያ ክር እንዲሰጡት ለተጠጋቸው ምክራቸውና ጸሎታቸውን ለጠየቀ ማንም ግለሰብ (ትግሬ ነው፣ አማራ ፣ ኦሮሞ ነው፣ ከምባታ ፣ጉራጌ ነው፣ ወላይታ ፣...) ሳይሉ የነገረ መለኮቱን ምስጢር አመሳጥረው በመተንተን ድነው የሚያድኑ፣ ተምረው የሚያስተምሩ፣ወደር የማይገኝላቸው የክርስትና ኣባት ነበሩ። “ያላወቁ አለቁ” ይላል ያገሬ ሰው። ብፁዕነታቸው በሕይወት በነበሩበት ጊዜ ቅድስናቸውንና የተሰጣቸውን ሀብተ መንፈስ ቅዱስ የተረዳላቸው ግን በጣም ጥቂቱ ሕዝብ ነበር። ያ ጥቂት ሕዝብም በጸሎታቸውና በቡራኬአቸው ተጠቅሞባቸዋል።

ይህች አጭር ጽሑፍ ለማቅረብ ያነሳሳኝ ነገር ቢኖር የብፁዕነታቸው የሕይወት ታሪክና መንፈሳዊ ተጋድሎ ገድል ለመጻፍ አይደለም። የብፁዕ አባታችን የሕይወት ታሪክና መንፈሳዊ ተጋድሎ ለዛ ባለው ብዕር ሊያቀርቡልን የሚችሉ ብቃቱ ያላቸው ሌሎች ታላላቆች ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ስላሉ ይህን ሥራ ለእነርሱ እተወዋለሁ።

እኔ ግን ዛሬ ለመጻፍ የፈለኩት ስለ ሲያትል ቅዱስ ገብርኤል ካህናትና ምዕመናንን መልካም ሥራን ነው።

ወገኖቼ!

እነዚህ ከትልቁ ባሕር (ኢትዮጵያ) በጥቂቱ የተቀዱ ወገኖች፣ የተፈጠሩበትን ሀገርና ምድር የሚያስከብሩ፣ ልባቸውንና ወሰናቸውን የሚያውቁ ወገኖቻችን የብፁዕነታቸውን መንፈሳዊ ጣእም ተረድተው የሚሰጥዋቸውን አባታዊ ትዕዛዝ አክብረው ቤተ ክርስቲያኗን ያለ ምንም የባንክ እዳ አንፀው በሰው ሀገር የወለዷቸውን ልጆቻቸውን የትውልድ ቋንቋቸውን አስተምረው ለራሳቸው ብቻ ሳይሆን በስደት ላለው ለመላው ኢትዮጵያዊ ሁሉ መኩሪያ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ።

የነዚህ ወገኖች ታሪካዊና መንፈሳዊ ሥራ ለብዙ ጊዜ በብፁዕ አባታችን በኩል በጆሮዬ ስሰማ ኖሬአለሁ። በአባታችን በሞት መለየት ምክንያት በሥፍራው ተገኝቼ በዐይኔ ያየሁትን ለመመሥከር እገደዳለሁ።

የብፁዕነታቸው ዜና እረፍት ከተሰማበት ቀን ጀምሮ ከየክፍለ ዓለማቱ ወደ ሲያትል መጉረፍ የጀመረው ምዕመናን ብዛት ቁጥር በቀላሉ የሚቆጠር አልነበረም። ይህንን ሁሉ ከየአቅጣጫው የመጣውን ካህናትና ሕዝበ ክርስቲያን ማስተናገድ ደግሞ ራሱን የቻለ ምን ያህል ከባድ ኃላፊነት እንደሆነ መገመት አያዳግትም። ለካህናቱና ለምዕመናኑ ቁርስ ምሳና እራት ማዘጋጀት ከግብር በኋላ ማፅዳት እንደገና ለሚቀጥለው ቀን የሚሆን ምግብ ሲያዘጋጁ ማደር ወዘተ በሌላ የሥራ ክፍል ደግሞ በብፁዕነታቸው የአሸኛኘት ሥነ ሥርዓት በተቀላጠፈ መልክ ለማዘጋጀት ከቀብር አስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶችና ከልዩ ልዩ የመንግሥትና የግል ድርጅቶች አካሎች ጋር ግንኙነት በማድረግ ፕሮግራም በማውጣት ልዩ ልዩ በራሪ ወረቀቶችን ፎቶግራፎችን በማዘጋጀት በሌላው የሥራ ድርሻ ደግሞ ከተለያዩ ክፍለ ዓለማት የመጡትን እንግዶች ምረፊያ ቦታ በማዘጋጀትና የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲያገኙ ማቀናጀት... እረ ስንቱ ድንኳን መትከል፣ ወንበር መደርደር፣ ይህ ነው የማይባል ከፍተኛ የሥራ ድርሻ ሲወጡ ከርመዋል።



ወገኖቼ!

እኔን ያስደነቀኝና እነዚህን ወገኖቻችንን በታሪክ ፊት እንዳይረሱ ያስፈልጋል ለማለት ያስደፈረኝ ይህን ሁሉ ሥራ ሲሠሩ የእርስ በርስ መጨቃጨቅ ወይም በኃይለ ቃል መነጋገር አላየሁባቸውም፣ ሁሉም በበጎ ፈቃደኝነት የተመደቡበትን የሥራ ድርሻ በፀጥታና በትሕትና ሲሠሩ ነው የተመለከትኩት።

ማርን የሚያህል ለሰው ልጅ የሚጠቅመውን ጣፋጭ ምግብ የምታመርተው ንብና ሰራዊቷ እያንድንዳቸው የተመደቡበትን የሥራ ድርሻ በብቃት ለመወጣት በሕረት ስለሚጓዙና ስለሚሠሩ ጣፋጭ ምርት ለሰው ለጆች ሊያቀርቡ ችለዋል።

እነዚህም የሲያትል ቅዱስ ገብርኤል ካህናትና ምዕመናን ከልብ የሚወዷቸውን አባታቸውን ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስን የመሰለ ታላቅ መንፈሳዊ የዘመኑ ሐዋርያ በሚያስደንቅ ግርማ በመሸኘት እንኳን እኛ ኢትዮጵያውያን የሀገሩን ተወላጆች አሜሪካውያኑንም ያስደነቀ ሥራ ሲሠሩ ታይተዋል።

“አባቱን አክባሪ ትውልድ” ማለት ይህ ነው የተወደዳችሁ ወገኖቻችን እግዚአብሔር በሁሉም ነገር ይባርካችሁ ዘንድ የሁላችንም ምኞት ነው።

ወገኖቼ!

ታዲያ እነዚህ ወገኖቻችን ባደረጉት መልካም ሥራ እኛ ፍጡሮች እደዚህ የተደሰትን፣ የዓለሙ ጌታ ፈጣሪማ እንዴት ይደሰት? ከነዚህ የተባረኩ ሰዎች የምንማረው ብዙ ትምህርት አለ፤ መደማመጥ፣ መከባበር፣ ወገናዊ ፍቅር ማሳደር፣ ለሃይማኖትና ለታሪክ መልካም ሥራ ሠርቶ መገኘትና፤ የመሳሰሉት ናቸው።

እኛ ኢትዮጵያውያን ወንድማችን ወይም እህታችን ከአጠገባችን በሞት ድንገት ሲለዩን ለጊዜው እንደነግጣለን ወዲያው ከዛሬ ጀምሮ ጥሩ ሰው ሆነን የእግዚአብሔርን መንገድ ለመከተል ህጉን ለማክበርና ለመኖር ቃል እንገባለን። ቃል መግባት ብቻ አይደለም የአቋም መግለጫ እና ወጣለን። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ውለን አድረን ያወጣነውን የአቋም መግለጫ ቀለሙ ሳይደርቅ ወደ ቀድሞው ክፉ ሥራችን እንመለሳለን።

ውድ ወገኖቼ!

ይህ አስከፊ ባሕሪያችን ግን ከእኛ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መወገድ ይኖርበታል።

ብፁዕ አባታችን በሕይወታቸው በነበሩበት ጊዜ በየቦታው እየዞሩ ያስተማሩን ነገር ቢኖር ሰው ሆነን ለቁም ነገር እንድንበቃ ነው። ያለበለዚያ አንዱንም ጠቃሚ ነገር ሳንይዝ አጓጉል ወድቀን እንቀራለን።

የተከበራችሁ ወገኖቼ!

ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ዕድገትና መስፋፋት በሀገርም ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ያደረጉት አስተዋፅዖ በሚዛን የሚለካ አይደለም።

እኚህ ታላቅ መንፈሳዊ አባት ተወልደው ባደጉበት፣ ያለምንም ረዳት ወጥተው ወርደው፣ ተምረው ባስተማሩበት፣ ለአንዲት ኦርቶዶክሳዊ ተዋህዶ ሃይማኖታቸው መስፋፋት የቤተ ክርስቲያን ዕድገት ሌት ተቀን በደከሙበት ሀገራቸው ላይ በሰላም ለመኖር በገጠማቸው ሰው ሰራሽ ችግርና በደረሰባቸው ከአቅም በላይ የሆነ ውጣ ውረድ ምክንያት ከሀገራቸው ተሰደው በመውጣት ወደ ሰሜን አሜሪካ ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ በዓላማቸው ፀንተው የቆሙ ስደተኛውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ያፅናኑ ከእስቴት እስቴት አድካሚ ጉዞ በማድረግ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ አብያተ ክርስቲያናት እንዲስፋፉና ራሳቸውን እንዲችሉ ጥረት ያደረጉ ታላቅ የፍቅርና የትህትና መምህር ነበሩ።

ብፁዕ አባታችን መኖሪያቸውና መንበረ ጵጵስናቸው ሲያትል ቅዱስ ገብርኤል ይሁን እንጂ በጠቅላላ በአሜሪካን ግዛቶች፣ በካናዳ፣ በአውስትራሊያ፣ በአፍሪካ፣ በአውሮፓ በመዞር አባታዊ ግዴታቸውን የተወጡ የዘመናችን የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ ሐዋርያ ነበሩ።

ውድ ወገኖቼ!

ለዛሬ ጹሑፌን ከማጠናቀቄ በፊት ለእግዚአብሔር በሚቀርብ በንፁህ ጸሎተ ኃይል ይተማመኑ የነበሩት ብፁዕ አባታችን በጸሎት ኃይል ያደረጉትንና እኔ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ በግል የማውቀውን ታሪክ ላካፍላችሁ እወዳለሁ።

በሀገራችን በኢትዮጵያ በደርግ ዘመነ መንግሥት ብፁዕ አባታችን አቡነ ዜና ማርቆስ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በምዕራብ ኢትዮጵያ የወለጋ ክፍለ ሀገር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ሆነው አገልግለዋል። በዚህ በአገግሎት ዘመናቸው ከአውራጃ ወደ አውራጃ ከወረዳ ወደ ወረዳ እየተንከራተቱ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን በማሳነፅ፣ የፈረሱትን በማስጠገን፣ የሌሎች ዕምነቶች ተከታይ የነበሩትን ወንጌልን በመስበክ እንዲጠመቁና የመንፈስ ቅዱስ ሀብተ ፀጋ እንዲያገኙ በማድረግ፣ ምዕመናን እንዲበዙ፣ የስብከተ ወንጌሉን ክፍል በማዋቀር ያደረጉት መንፈሳዊ ተጋድሎ በቀላሉ የሚገመት አልነበረም።

ብፁዕነታቸው መንፈሳዊ ተጋድሏቸው የክርስቲያን ጠላት ከሆነው ዲያብሎስ ጋር ብቻ አልነበረም የኦርቶዶክስ ሃይማኖት እንዳይስፋፋ ልዩ ልዩ ሰው ሰራሽ ተንኮል በሚፈጥሩ በክፍለ ሀገሩ ላይ በሰፊው ተንሰራፍቶ በኖረው የፕሮቴስታንት ሃይማኖት መሪዎችና በሀገሪቱ መንግሥት ባለስልጣን በነበሩ የፖለቲካ ካድሬዎች ጋር ጭምር ነበር።

ታዲያ በአንድ ወቅት የተለመደውን የሀገረስብከት ሥራቸውን ለማከናወን ወደ ምዕራብ አውራጃ ተጉዘው በጊምቢ አውራጃ እናንጎ በተባለ ወረዳ ውስጥ የፈረሰ ቤተ ክርስቲያን በሚያሳድሱበት ጊዜ ይህችን ልዩ አጋጣሚ ሲጠብቅ የኖረና በብፁዕነታቸው ሥራ የማይደሰት አንድ የፖለቲካ ካድሬ ያልተጠበቀና ድንገተኛ ማዕቀብ ያደርግባቸዋል፣ ለክፉ ሥራ እንዲያመቸው ሹፌራቸውን በቀጥታ ትዕዛዝ ጠርቶ ወደ ሌላ አውራጃ ለፖለቲካ ሥራ የሚሔዱ ካድሬዎችን ይዞ እንዲሔድ ካደረገ በኋላ ብፁዕነታቸውን ካሉበት ከተማ እንዳይወጡ በማስደረግ ያለአስፈላጊ የሆነ ዘለፋና ሞራላቸውን የሚነካ ድርጊት ፈፅሞባቸዋል። ይህ ካድሬ ለዚህ አድራጎቱ የሰጠው ምክንያት አባታችንን ለኢትዮጵያ አብዮት ፀር ከሆኑ የድሮ የመሬት ከበርቴዎችና ባላአባቶች ጋር የጠበቀ ግንኙነት አላቸው የሚል ነበር።

ይህን ታሪክ ለእኔ ያስተላለፉት ወላጅ አባቴ በዚያን ጊዜ በቦታው ተገኝተው የዐይን ምሥክር የነበሩ ሲሆን ይህ በጭካኔውና በሰው ልጅ ገዳይነቱ የታወቀው ካድሬ የአባታችንን ሕይወት ለማጥፋት ወደኋላ የሚል አንዳልነበረ ሁሉም የተረዳውና ተስፋ ቆርጦ የተቀመጠበት ወቅት ነበር።

ብፁዕ አባታችን ይህ ሁኔታ እንደተፈጠረ በቤተ ክርስቲያን አጠገብ የነበረ መቃብር ቤት በመግባት ዘግተው ምግብ ከመብላት ራሳቸውን ገትተው ጸሎት ጀመሩ። አንዳንድ ግለሰቦች በድብቅ ሁኔታውን ወደ መንበረ ፓትርያሪኩ ፅህፈት ቤት አዲስ አበባ ጉዳዩን እናመልክትልዎ ሲሏቸው ፈቃደኛ ካለመሆናቸውም በላይ “እኔ የማመልከው አምላክ ይህንን ካድሬም ሆነ ዓለሙን የፈጠረ ጌታ ነው ፣ ታዲያ የእኔ ጸሎት ይህንን አንድ ደካማ ፍጡር ከዚህ መጥፎ ሥራው መለወጥ ካልቻለ የእኔ ድካም ሁሉ ከንቱ ነው ማለት ነው” በማለት በጸሎታቸውና በሱባኤአቸው ፀንተው ምህላቸውን ቀጠሉ። ከሁለት ሰባት በኋላ ልክ በአስራ አምስተኛው ቀን ይህ ሀገሩን ያንቀጠቀጠው የፖለቲካ ካድሬ እየበረረ ወደ አባታችን ወደ አሉበት መቃብር ቤት በመምጣት በሩን እንዲከፍቱ ይጠይቃቸዋል። በቦታው የነበሩ የዓይን ምሥክሮች እንዳሉት፣ “ይህ ሰው አባታችንን ወዲያው የሚገላቸው መስሎን ነበር” ነው ያሉት። ነገር ግን የተፈጠረው ሁኔታ ከሁሉም ሰው ግምት የተለየ ነበር። ግለሰቡ በአባታችን እግር ላይ ወድቆ “አባቴ ይማሩኝ፣ ለእርስዎ የማይገባዎትን ማጉላላትና በደል በመፈፀሜ ምክንያት በመንፈሴ ሌትም ቀንም ሰላም አጥቻለሁ። ይቅር ይበሉኝ፤ በማለት በእንባ ይታጠባል። አባታችንም በተለመደው የረጋ ትህትና የተሞላው ጠባያቸው ይህን ሰው “አይዞህ የክርስቲያኖች ጠላት የሆነው ዲያብሎስ ሊጠቀምብህ ያደረገው ስለሆነ አልቀየምህም፣ እግዚአብሔር ይቅር ይበልህ፣ እግዚአብሔር ይፍታህ፣ ወደፊትም የዚህ ዓይነት ክፉ ሥራ አትሥራ።” በማለት መልሰውለታል። ቀጥሎም ይህ ሰው ወደ ሌላ ሥራ የላከውን ሹፌራቸውን እስኪመጣ ድረስ ሳይጠብቅ ለአባታችን ሌላ ሾፌርና አጃቢ አዘጋጅቶ ወደ መንበረ ጵጵስናቸው፣ ነቀምቴ ከተማ በክብር እንዲመለሱ አድርጓቸዋል። በእውነቱ ለእግዚአብሔር የሚቀርብ ጸሎት ምላሹ ፈጣን ነው።

የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ በአንድ ወቅት አባታችንን አግኝቶ በዚያን ጊዜ ስለነበረው ሁኔታ ስጠይቃቸው እርሳቸው ግን ዝርዝር ውስጥ ሳይገቡ በጠቃላይ “ሁኔታው ሲፈጠር ወደ ፈጣሪዬ ጸለይኩ ያቀረብኩትም ጸሎት በጌታዬ መንበረ ፀባዎቱ ፊት ቀርቦ ወዲይውኑ የአፈጻጸም መልስ ተሰጠኝ” በማለት ለዛ ባለው አነጋገር መልሰውልኛል።

ውድ ወገኖቼ !

ልብ ብላችሁና አስተውላችሁ ከሆነ ብፁዕነታቸው ሲያስተምሩ በሰው ልጅ ላይ የሚደርሰውን ግፍና ጭቆና የማይሹ ሁልጊዜ ሰላምን የሚሰብኩ የትህትና አባት ነበሩ። በተጨማሪም ለሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንና ለሕግ እንድንታዘዝ ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን እንድናውቅና እንድናስከብር። በልዩ ልዩ እንግዳ ትምህርትና ተራ አሉባልታ እንዳንፈታ በያዝነው ዓላማ እንድንፀና በጸሎት እንድንተጋ እርስ በርሳችን እንድንከባበር እንድንዋደድና እንድንስማማ ይህንንና የመሳሰሉትን ምክርና መንፈሣዊ ትምህርት ሲሰጡን ቆይተው በሥጋ ከኛ ተለይተዋል ሆኖም በመንፈስ ዘወትር ከእኛ ጋር ናቸው።

በዓለም ዙሪያ ያሉትን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ የመንፈስ ቅዱስ ልጆቻቸውን ሁሉ እንግዚአብሔር ያጥናን።

በጸሎተ ፍትሀቱ ወቅት በብፁዕ አቡነ ሉቃስ በሲያትል ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን የበላይ ጠባቂ ሲነገር እንደሰማነው የብፁዕ አባታችን አቡነ ዜና ማርቆስ አፅም ያርፍበታል ተብሎ የታሰበውና በቅርቡ ይገነባል የተባለው በሂውስተን ቴክሳስ የሚገኘውን ገዳም ለሁላችንም ስደተኛ ኢትዮጵያውያን መታሰቢያና የታሪክ ወመዘክር ሊሆን ስለሚችል በጉልበት፣ በእውቀት፣ እንድንረዳ አስፈላጊ ነው ብዬ በግሌ አምንበታለሁ። እርግጠኛ ነኝ ሁላችሁም በዚህ የተቀደሰ ተግባር እንደምትሳተፉ ጥርጥር የለኝም።

የብፁዕ አባታችን ቡራኬ ይድረሰን!

አቤል አድማሱ


Tikam K. Lalla, LL.B.
• BARRISTER • SOLICITOR • NOTARY PUBLIC
•ኢሚግሬሽን •ቪዛ •የህግ ውክልና
• House Purchase/Sale/ Mortgages
• Wills • Incorporation • Business
• Immigration • Visa • Declarations
• Power of Attorneys • Notarizations
ቲካም ኬ ላላ፥ የህግ ጠበቃ
Toronto Main Office:
1203B Bloor St. W., Toronto, ON, M6H 1N4
(Between Lansdowne & Dufferin)
Tel: 416-532-2801 • Fax: 416-532-4942
email: tklalla@rogers.com
Mississauga Home office:
5159 Hidden Valley Court
(Eglinton & Creditview)
Tel: 905- 812-8004
(Evening & Weekends - By appointment only)

# ዓውደ -ሃሳብ

ይህ ዓምድ ከአንባቢያን የሚቀርቡ ወቅታዊና ዋና ዋና ጉዳዮችን ያስተናግዳል። የሐዋርያ አታዳሚዎች በየወሩ የሚስተናገዱ ጥያቄዎችን፣ ሃሳቦችንን አማብራሪያ መልሶችን በማቅረብ ትሳተፉ ዘንድ የዓምዱ አእዘጋጅ ያሳስባል።

## መጪውን የግንቦት ምርጫ መካፈል ወይስ አለመካፈል ይበጃል?

ከአበበ ዋሲሁን

ይህ በምርጫው መሳተፍና አለምሳተፍ ብዙ የተባለለትና ያከራከረና ያጨቃጨቀ ርዕስ ነው። በእኔ አስተያየት የመጪውን የግንቦቱ 2002 ዓ.ም ምርጫ መካፈል ይበጃል ወይም አይበጅም ከማለታችን በፊት የአገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ መመርምሩና ጥቅምና ጉዳቱ መለየትና መመዘን አስፈላጊ ይመስለኛል። ከዚያ ይኸናው ይበጃል ለማለት በመካሄድ ላይ ያለውን የሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ትግል ምን ያህል ይረዳል ምንስ ያህል ይጎዳል የሚለውን በቅጡ ማጤን ይገባል ባይ ነኝ።

በአሁኑ ወቅት ድፍረት ካልሆነብኝ የሚስማኝ በአገራችን ላይ ከአንዣበብን አደጋ ለማውጣት ስመለከተው የተቃዋሚ ድርጅቶችና አመራሮች ታግለው ሕዝባችን ለማታገል በብቃት የተዘጋጁ አይመስለኝም። ሕዝባችን ምን ያህል አደራጅተዋል? ከአለፈው የ97ቱ ምርጫ ምን ትምህርት ወስደዋል? ሕዝባችን አሁንም የመሪ ያለህ እያለ እየጮኸ ነው። ለዚህ ጥያቄ በእርግጠኝነት አጥጋቢ መልስ ይዘው ቀርበዋል? እነዚህ ጥያቄዎችና ሌሎች ያልጠቀስኳቸውን ጨምሮ አድበስብሶ ለማለፍ መሞከር "አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ" ነው የሚሆነው።

በበኩሌ በእኔ እይታ ማለት "ነፃና ፍትሐዊ" በሌለበት በአምባገነን ሥርዓት ውስጥ የመጪውን ምርጫ እንካፈላነንና አንካፈልም የሚሉትን ወገኖች አቅዋም እኔ እንደተረዳሁትና እንደገባኝ እንደሚከተለው ነው።

በምርጫው እንሳተፋልን የሚሉት

እነዚህን በምርጫው ያለበቂ ዝግጅት እሳተፋለን የሚሉት ድርጅቶችን በሁለት ከፍዬ ለማየት ጥረት አደርጋለሁ። አንድኛው የምርጫ ድርጅቶች ነን የምርጫ ስነሥርዓቱ ባንፈርምም እንኳን የፈለገው ይሁን ወይም ግራም ነፈስ ቀኝ በምርጫው እንሳተፋለን ብለው የወሰኑ ናቸው። ሁለተኛው ጎራ ያሉ ድርጅቶች በምርጫው ካልተሳተፍን የድርጅት ሕጋዊነታችን እንናጣለን ስለሆነም ያለን ብቸኛ አምራጭ በምርጫው መሳተፍ ነው ይላሉ። በፈረንጆች አደራዳሪነት የምርጫ ስነምግባር ለማክበርና ለማስከበር ከአምባገነኑ መንግስት ጋር በመፈራረም ዋስትና አግኝተናል ባዮች ናቸው። እደማየው የአምባገነን መንግስት በአሁኑ ጊዜ የራሱንም ጥላ የማያምን በመሆኑ በምርጫው እንካፈላለን ላሉት ቃል ከገባላቸው የፓርላማ መቀመጫ ውጭ እንፈራገጣለን ቢሉ ምንም ዓይነት እርምጃ ከመውሰድ ወይም ከማድረግ እንደማይመለስ እያሳየ ነው። የተቃዋሚ ድርጅቶች ለምርጫው ባቀረቧቸው እጩዎች ላይ ከግድያ እስከ ማስርና ማስፈራራት በካድሬዎች እየደረሰባቸውና እየተፈጸመባቸው ነው።

በምርጫው አንሳተፍም፡

እነዚህ ወገኖች በመጭው ግንቦት ምርጫው መሳተፍ ፋይዳቢስ ነው። አለመሳተፍ ማለት ማዕቀብ በማድረግ አባገነኑን አገዛዝ ብቻውን ሮጦ ብቻውን እንዳሸነፍ ደጋፊዎቹና የአለም ህብረተስብ ይወቁት ማለት ያለ አጃቢ ወይም አድማቂ አሸናፊ ነኝ በማለት በያዘው አባገነናዊ አገዛዝ ይቀጥላል ማለት ነው። ዋና መከራከሪያቸው ቢያንስ በቅድመ ሁኔታ የተቃዋሚ የፓለቲካ ድርጅቶች መሪዎችና አባሎች እንዲሁም ደጋፊዎቻቸው ከ35 ሺ በላይ በእስር ቤት ታጉረው እያሉ ያንን ረግጦ ምርጫ መግባቱ ትክክል አይደለም። አባገነኑ መንግስት አራት ዓመት ሙሉ የራሱ የምርጫ ቦርድ ሲያጠናክር፡ የራሱን የምርጫ ታዛቢና ቆጣሪ በማዘጋጀት እንዲሁም ሁሉን ቀዳዳዎች ለተቃዋሚዎች እንዳፈናፈኑ በፀረ ሽብርተኛ ህጎች በመሳስሉ ወጥመድ አዘጋጅቶ ከዚህ በተጨማሪ ከ5 ሚሊዮን በላይ በጥቅማጥቅም አባሎች መልምሎ የፓለቲካ ምህዳሩን ለተቃዋሚዎች አጥብቦ እስቲ ማን ይደፍረኛል በሚል ሆኔታ ውስጥ ዘሎ መግባት እንኳን መስረታዊ ለውጥ ማምጣት ቀርቶ ጥገናዊ ለውጥ ለማምጣት ያለው እድል በጣም ጠባብ ነው ስለሆነም ትግሉ መሆን ያለበት አምባገነኑን አገዛዝ ማስወገድ ነው የተቃዋሚ ድርጅቶ ሚና መሆን ያለበት ያላሉ።

የእኔም የግለስብ የደረስሁበት አቅዋም በመጭው ምርጫ መሳተፍ ክጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል የሚል ነው። የተቃዋሚ የፓለቲካ ድርጅቶች ታሪካዊ ተልዕኮ መሆን ያለበት ተባብረውና ሕዝባችንን አስተባብረው አገራችን ከጥፋት ማዳንና የዴሞክራሲያዊ ስርአት መመስረት ተቀዳሚ ተግባራቸው ሊሆን ይግባል ባይ ነኝ። በዴሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ ይህ እንዳሁኑ ፋይዳቢስ ምርጫ ሳይሆን የብዙሃን የፓለቲካ ፓርቲዎች በነፃና ፍትሃዊ መንገድ በፕሮግራማቸው ተወዳድረው አሸናፊው ፓርቲ ሕዝባችን ለተወስነ ጊዜ ያገለግላል የሚለው አስተሳስብ ለእኔ ትርጉም ያለውና ውጤታማ እርዐይ ነው።

TANA PRINTING ENT.
ጣና ማተሚያ ቤት
ማንኛውንም የህትመት አገልግሎት በየትኛውም ቋንቋ እንሰጣለን።
Complete Printing & Copy Services Including Wedding Invitations
2,500 Full Color Business Cards (Both Sides) $125
5,000 Full Color Business Cards (Both Sides) $199
10,000 Full Color Business Cards (Both Sides) $375
Limited time offer
633 Vaughan Rd. Toronto ON. M6C 2R4 (Vaughan & Oakwood)
Tel: 416.654.2020
Fax: 416.653.6191
e-mail: print@tanaprinting.com
website: tanaprinting.com

LAW OFFICE
JOSEPH OSUJI
B.A (Hons), LLB
Barrister, Solicitor & Notary Public
The Law office is accepting new clients for:

- Criminal Law
- Police Complaints
- Family Law
- Immigration law
- Refugee Law
- Civil Litigation
- X Human rights/Discrimination.
- Business/commercial Law
- Native Law
- Coroners' Inquests
Fearless, Aggressive, Fight To Win Justice
Cell: 416-559-1418
Office: 647-349-5225
Fax: 647-349-5355

# THE OPENING OF SPICE GARDEN RESTAURANT

**Chef Vishwanath Gord speaks to our correspondent Jatin Naik on the opening of his new Restaurant in Brampton**



Jatin Naik
njatin@yahoo.com

*Where do you come from in India?*

"In India, I was born in Nainital, Uttrakand. I have been cooking since the age of 12. Later on, I came to Mumbai to make a new beginning and started working with Pritam Group of Hotels. Soon with my hard work, I rose to the top. I use to prepare different kinds of dishes".

*What kind of cuisines do you specialize in?*

"My speciality is Indian & Chinese food. My most popular dishes are Butter Chicken, Goat Curry, Hyderabadi Biryani, Shikari Kebab, Chinese – Chilli Chicken and Chicken Manchurian, Hakka noodles and Fried rice. And amongst vegetarian dishes are Veg – Muglai Paneer, Malai Kofta. Palak Panner and Palak Masala. Naan and Amritsari Kulcha".

*When did you come to Canada?*

"I came to Canada in December2003. I am living in Canada since the past 6 years. Recently, an idea struck me. A restaurant without a good chef is no place to be! So I planned to open a new restaurant by bringing together the best chefs in Toronto area and achieve my dreams".

*When are you starting the new restaurant, tell us something more on it.*

"Recently, I came up with this idea. I saw a place in Brampton and I gathered some chefs. We had an initial meeting where I shared my idea to all the chefs and they were receptive and responsive to my thoughts. We agreed to form a company with a set number of people. We invited chefs as shareholders. The benefit here would be that the profits each person would earn would be in the same proportion as how much they invested as a shareholder".

*How do you plan to carry forward the restaurant?*

"I am the advisor, shareholder and the main Chef of this restaurant. We purchased the restaurant. My food quality would not match the restaurant so we broke the restaurant in order to renovate it. I had a dream of opening my own restaurant and that time has come close to fruition! However, we had a number of challenges on the way"

*How did you overcome all those challenges?*

"I came across many hurdles but I was determined to overcome all the problems. I had gathered over 10 chefs plus 2 restaurant owners to support me and we are now close to opening the restaurant. And although we had many challenges every step of the way we have all worked unitedly very hard. We are determined to make it a success by helping each other. We are inviting all senior citizens and children free for one day and rest at 20% discount at the opening so all will be welcome. We will provide the exact date soon.".

*And where is the restaurant located?*

"We are calling the restaurant 'Spice Garden'. Its located at Shoppers World mall in Brampton at the major intersection of Steeles and Hurontario. We have a very good location with so many businesses, residences, malls and shops in the vicinity. We are getting some very good response from the people. This is a central location. With our hard work we are determined to make it a success!"

*What will be the speciality of this new restaurant?*

"Quality food at reasonable rate. Bar and Tandoor place will have a new look. We are planning to have a open glass Tandoor where people can actually watch the chefs whirling 'Roomali Roti' and preparing 'Tandoori Roti' or 'Kulchas' and the bar will be unique and have Dhaba feel in its outlook. Other things would be: Fine dining, tile flooring, Indian ethnic style decoration, Dhaba feel at places, Veg, non-veg food will be served. Sweets and a special Indian Espresso coffee are the other features. We are also having a Party & Banquet hall in the next room. We are bringing speciality Handi Buffet as in olden times from India. For this we are bringing authentic handis from India. Food will be served as Buffet and 'a la carte'. Hyderabadi Biryani will be a speciality and cooked and done in oven. And now, its time for the opening!"





# ቀውሱ ከሚያረግብ ጊዜ ላይ አልደረስንም

ነጋ ጠባ ቀውስ ውስጥ ተዘፍቆ ግን ከማጡ መስመጡ አልታይ የሚለው አገዛዝ መጨረሻው የሚያምር አለመሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ወያኔ ከ1983 ጀምሮ ማለትም ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ ከቀውስ ወደ ቀውስ እየተሸጋገረ ፤ ከድጡ ወደ ማጡ እየሰመጠ- መሄዱን ሕዝብ ሁሉ እያየው ያለ ሀቅ ነው፡፡ ወያኔ ትግል ጀመኗኩ ሲል ጀምሮ በሕዝብ ጥላቻ ተቃኝቶ በተለይ የሸዋ አማራ በሚለው ሕዝብ ላይ ሲያጓራ የከረመ መሆኑ የሚታወቅ ነውኝኝ ትግላችን ፀረ አማራ ነው ብሎ በይፋ የለፈፈው ይህ የመለስና የስብሐት ነጋ በጥላቻ የሰከረ ቡድን ወደ ስልጣን ሲጓዝ የብዙ ሺ ዜጎችን ደም አፍሶ፤ ሀገርንም አስለቅሶ፤ በሀገር ወዳዶች ላይ ተረማምዶ፤ ረሀብተኛውን ለሞት ዳርጎ፤ የራሱንም አባላት ጨፍጭፎና አሳዶ፤ ለባዕዶች ሰግዶና ኢትዮጵያን ገና ሳይዛት ቸብችቦ እንደነበር

የሚደበቅ አይደለም፡፡ ለሥልጣን ከበቃ ጊዜም ጀምሮ ሀገርን ለግንጠላ አጋልጦ፤ ጠባብ ብሄረተኛነትን አንግሶ፤ የሕዝብን መብት ረግጦ፤ ግራ ቀኙን ረሽኖና አሳዶ፤ በፈረደባት አማራ ላይ ዘምቶ፤ ሌሎችንም በተራ ተራ በጠላትነት ፈኗጆ፤ በአደባባይ ኢየሱስ፤ አንዋር መስጊድ፤ በወተርና አርባጉጉ፤ በአሰቦትና በምስራቅ ወለጋም ከአጋሮቹ ጋር ሆኖ በንፁሃን ደም ታጥቦ፤ ሀገርን በጭፍንና

በጭካኔ ዘርፎ፤ የአንድ ብሔረሰብ የበላይነትን አስፍኖ ግን ዓይኑን በጨው አጥቦ ዴሞክራሲን አሰፈንኩ ብሎ መመፃደቅ መቀጠሉንም ታዝበናል፡፡ መድብለ ፓርቲ ሥርዓትና ምርጫ የከበርቴው ጫጫታ ነው ሲል የነበረው ወያኔ ለጡት አባቶች ይህንኑ መድግም ተስኖት ምርጫ ምርጫ እያለና በተለጣፊ ታጅቦ እየተውገረገረ ምረጡ ቢልም ሁሉም ነገር ቧልት መሆኑ ደግሞ በተደጋጋሚ ከመጋለጥ አላመለጠም፡፡ የወያኔ ምርጫ ከደርጉ ምርጫ በይዘትና መሰረት እምብዛም ሳይለይ ቆይቶ በ1997 ሕዝብ በድምፁ ውድቀትን ሲሰጠውም በጭፍጨፋና በጉልበቱ ህገ ወጥ ስልጣኑን ቀጥሏል፡፡ ነፃ ጋዜጦችን ዘግቷል፤ ከ30ሺ በላይ የፖለቲካ እስረኞችን አግቷል፤ ብዙዎችን ደብዛቸውን አጥፍቷል፤ ሀገርን በጭካኔ ዘርፏል፤ ሕዝብን በረሀብ አለንጋ ገርፏል፡፡

19 ዓመት ሙሉ ቀውስ ተረጋግቶ በስልጣን መቀመጥን አያመለክትም፤ ጭንቅና መራድን እንጂ፤ ወያኔ እርስ በርሱም ተከፋፍሎ ፍፁም ሥልጣን በግብዙ አምባገነን መለስ ዜናዊ እጅ ገብታለች፡፡ የአገዛዙ ህብረተሰባዊ መሰረትም ጠቦ ዛሬ ከክልል አንድ የመጡ ከበርቴዎች፤ አምራች ሳይሆኑ አቀባባይና ዘራፊ ከበርቴዎችና ተለጣፊ ፍርፋሪ በላተኞችን አቅፎ እርቃኑን ቀርቷል፡፡ ገዢው መደብ የሳሳ ነው፤ ዘረኛም ነው፡፡ በየክልሉ የኮለኮላቸው አዲሱና አባዱላዎቹ ደግሞ የራሳቸው ህልውና የሌላቸው የወያኔ የቀትር ጥላ ሆነው የባጁ ናቸው፡፡ ይህ አቀባባይና የመንግስት ሥልጣንን መሰረት ከበርቴ ለወያኔ አገዛዝ በቂ መሰረት ሊሆን ባሌመቻሉ አገዛዝ መመኪያው የጦርና የአፈና ሀይሉ ነው፡፡ ይህንንም በክልል አንድ ተወላጅ መኮንኖችና ሀላፊዎች ሥር በማድረግ ታዛዥነቱን ለማረጋገጥ ይጥራል፡፡ ግን ይህ ጠባብ መሰረት በመሆኑ የራሱ የወያኔ ጦርና የአፈና ተቋም በሕዝብ ፈራሽ ሆኖ ለአገዛዙ ዘላቂ መከታ ሊሆን የማይችል ነው፡፡ በዚህም ረገድ ተቃዋሚ ሀይሎችና ሕዝብ በስልት ወታደሮችና መኮንኖችን ከወያኔ ለመነጠል ያልተቋረጠ ጥረትና ቅስቀሳ ማድረግ ይጠብቅባቸዋል፡፡ በመጪው የወያኔ ምርጫ ወያኔ በመሰረቱ በራሱ ሮጦ/ ተወዳድሮ ራሱ አሸናፊ ሆኖ መውጣቱ የማያከራክር ቢሆንም ሂደቱ የመለስን ቡድን በመጠኑም ቢሆን እየጎረበጠው መሆኑ የሚታይ ነው፡፡ አቅፈውና ድግፈውት የቆዩት ምዕራባውያን የአምባገነኑ ድርጊት በአደባባይ የሚደገፈ አልሆን እያላቸው ትችትን ማከታተል መጀመራቸው ለወያኔም የተደበቀ አይደለም፡፡ በአንፃሩ ግን ጫኑኝ ባይ መጋዣቸው በመሆኑ በሀገር ወዳዶቹ ሊተኩት ፍላጎቱም ከቶ የላቸው ማለት ይቻላል፡፡ ነገር ግን በመጠኑም ቢሆን ሲተቹት መርበትበት ልምዱ ነውና የሚናገረውና የሚቀበጣጥረው ይበልጥ ለትዝብት ይዳርገዋል፡፡ ባለፈው ሰሞን የአሜሪካኖችን ፕሮፓጋንዳ በሚያሰራጨው ራዲዮ ላይ ያሰማው ዘለፋና አግደዋለሁ ዛቻ በምሳሌነት የሚጠቀስ ነው፡፡ ድንጉጡ ወያኔ የፍኖተ ራዲዮን ቢያንስ በአዲስ አበባ እንዳይሰማ በቻይና እርዳታ ማገዱ በዚህ የሚጠቀስ ነው፡፡ የወያኔ ቀውስ ከመሰረታዊ ሀገርና ሕዝብ ካጂነቱ ጋር የተያያዘ መሆኑ ደግሞ ለዓመታት የታየ

ጉዳይ ነው፡፡ ሀገሬን ገንጥሉልኝ ብሎ ባዕዳንን የተማፀነ የአንድ ሀገር መንግሥት ይጠቀስ ቢባል ይኸው የወያኔ ሀፍረተ ቢስ ቡድን የሚጠቀስ ይሆናል፡፡ ሕዝብን በብሄረሰብና በሀይማኖት ከፋፍሎ ለማጫረስ ይሁነኝ ብሎ ቀን ተሌት የሚዳክር አገዛዝ ይኸው የወያኔው ነው፡፡ ሥነ ምግባር የጎደላቸው ዋልጌዎችና በሙሰና የተጨማለቁ ግለሰቦች የታጨቁበት ይህ ገዢ ቡድን ሀገርን የሚያሳፍርና የሚጎዳ ነው፡፡ መለስ አልን÷ ስብሐት አልን÷ ስዩም ወይም አዜብ ሁሉም በነቂስ ተራ ዘራፊዎች፤ ሥነ ምግባራቸው ውድቅና ብልሹ የሆኑ ናቸው፡፡ እንኳን ኢትዮጵያን የመሰለች ክቡርና ባለታሪክ ሀገር መንደሬርም በስርዓት ሊያስተዳድሩ የሚችሉ አልነበሩም/አይደሉምም፡፡ ይህ በሕዝብና በሀገር ላይ የመጣ መርገም ይሉኝታም ግብረገብም የለውምና፤ ሕዝቤ የሚለውን ሳይቀር ሲራብ ለሞት የዳረገ አረመኔ ቡድን ነውና፤ በሀይል ከስልጣን ካልተወገደ የሕዝብን ፍላጎትና ጬኸት አድምጦ ገለል የሚል አይደለምኝኝ ለዚህም ነው በሁለገብ ትግል መቆሚያና መቀመጫ አሳጥቶ እንጦርጦስ ማውረድና መቅበር የግድ የሚሆነው፡፡ የወያኔ ቡድን ፀረ አርሶ አደር በመሆኑ አብዛኛውን የኢትዮጵያ ሕዝብ እየበደለ ያለ መሆኑ ይታያል፡፡ ለም መሬቶችን ከጎንደርና ወሎ ቀምቶ ወደ ክልሉ አስገብቷል፡፡ በእርሻውም ኤኮኖሚ በበላይነት ተሰማርቶ አምራቹን ያደኸያል፡፡ አርሶ አደሩም የመሬቱን ባለቤትነት ተነጥቆ ለወያኔ ዘረፋ ሰለባ ሆኖ በመሰቃየት ላይ ነው፡፡ ይህ ያልበቃ ይመስል ወያኔ የሀገራችንን ለም መሬት ለባዕዳን እየቸበቸበና ገቢውን ወደ ራሱ ካዝና እየከተተ ነው፡፡ የለመደበት ዋሾ መለስ ዜናዊ ይህንን የከሀዲ ሥራ ለመሸፋፈን ለባዕዳን የተሰጠው መሬት ማንም ያልሰፈረበት ምድረበዳ ነው ቢልም አርሶ አደሩ መሬቱን እየተቀማ ያለ መሆኑ ሊካድ የሚችል ሃቅ አይደለምኝኝ ከዚህ በተያያዘ ከሁሉም የከፋው ደግሞ በአባይ ወንዝ ምንጭነቷ የተነሳ ኢትዮጵያን ለመውረር፤ ለመከፋፈልና ለማዳከም ዕድሜ ልክ ለጣረችው ግብፅ በአባይ ምንጭ አካባቢና በአፋር መሬት ሰፊ መሬትን መሸጡ ነው፤ የክህደት ክህደት፡፡ የወያኔ መሪዎች የሰናፍጭ ቅንጣት ታህልም ኢትዮጵያዊነት ስሜት የሌላቸው መሆናቸውን በዚሁ ድኗጊታቸው ራሳቸውን አጋልጠዋል፡፡

ከአሰከፊው ወደ አስከፊው ስንጓዝ ደግሞ በተለይም የዚህን ፀረ ኢትዮጵያ ቡድን ማንነት የሚያጋልጠው የሀገራችንን መሬት፤ የስንት ጀግና ደም ፈሶ ተከብሮ የነበረውን መሬት-- ለሱዳን አሳልፎ መስጠቱ ነው፡፡ የወያኔው ፈላጭ ቆራጭ ሲዋሽ ከሱዳን ጋር ገና ድንበር/መሬት አልተካለልንም ሲል የተደመጠ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የተሰጠው መሬት ድሮም የሱዳን የነበረና ማንም ኢትዮጵያዊ ያልሰፈረበት ብሎ ቀጥፏል፡፡ ሱዳን ተሰጠኝ ብሎ የሰፈረበት የቋራ መሬት ላይ

ኢትዮጵያዊ አርሶ አደሮችና ዘመናዊ እርሻ ባለቤቶች ይንቀሳቀሱበት ነበር፡፡ ዛሬ ሱዳን ሰፍሮበት ነፍሶ ገበያ ተራራን ማዕከሉ አድርጓል፡፡ ይህን ክህደት ለማለሳለስና ለማረሳሳት በወያኔ የተቀጠሩ አደናጋሪዎች በሀገር ቤትም በውጭ ሀገርም በስልት እየተንቀሳቀሱ ናቸው፡፡ ግን ሊረሳ የማይችል ክህደት ነው፡፡ በሀገራችን ታሪክ ተሰምቶና ታይቶ የማይታወቅ ክህደት ነውና ሕዝብ ይህንን ጉዳይ በአቢይ ደረጃ አስቀምጦ ከሀዲው ቡድን ላይ አምርሮ መነሳት አለበት፡፡ ከሕዝብ ጭቆናና ብዝባዛ ባሻገ ሀገርን መሸጥና አሳልፎ መስጠት ነውና በቀላሉ የሚታይ አይደለም፤ ሊሆንም አይችልም፡፡ ለወያኔ አመቻችቶ የሰጠው ያለፈው አረመኔ አገዛዝ ለመሆኑ ምንም ምርምር ጠያቂ አይደለም፡፡ ለሀገር የቆመውን ትውልድ በሽብር ፈጅቶ፤ ሕዝብን አሸማቆ፤ ህብሬ ብሄር ድርጅቶችን አዳክሞ ለጠባቦች በር ከፍቶ የወደቀው የኮለኔሉ አገዛዘ በታሪክ ሁሌም ተጠያቂና ተወቃሽ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ከራስ ባለይ ነፋስን፤ ግለኝነትን፤ ፍርሀትን አንግሶ ያለፈ አገዛዝ ለወንበዴው የወያኔ አገዛዝ ሕዝብን ሰለባ አደረገው፡፡ በመሆኑም ህሊናቸውንና ሰብዕናቸውን ለወያኔ በሊዝ የሸጡ ምሁሮችና ሆድ አምላኩዎች ፈልተው፤ የሕዝብን አንድነት ተቃርነው ጠባብነትን ያቀፉ ተፈልፍለው ሕዝብና ሀገርን ሊፈታተኑ ችለዋል፡፡ ዛሬ የወያኔን አገዛዝ በጋራ ለመታገል ጋሬጣ የሆነው ይህ ሁኔታ ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡

ወያኔ ሀገርን ሕዝብንም ሸጦ ባዕዳንን ለማቀድ ችሏል፡፡ በዝርፊያ የተሰማሩት እነ ቻይና መሰሎቹ ወዳጆቹ ናቸው፡፡ የራሳቸውን ተልዕኮ ለማሟላት የኢትዮጵያውያንን ደም ያስፈሰሱት ምዕራባውያን፤ በተለይም አሜሪካ፤ በወዳጅነት ማቀፍ ብቻ ሳይሆን ሙለ በሙሉ እያገዙት ናቸው፡፡

መሬት የተለገሰው ሱዳንም እንዲሁ ለወያኔ አጋር ሆኖ ስደተኞችንም ሲበድልና ሲያሰቃይ ይገኛል፡፡ ሆኖም የወያኔ ፍላጎት የተሟላ አይደለም፡፡ በሶማሊያ ገብቶ ሽንፈትን ቀምሶ ተመልሷል፡፡ ሱዳንም በራሱ ውስጣዊ ቀውስ እየታመሰ ነው፡፡ የአፍሪካ ቀንድና የቀይ ባህር አካባቢ ሰላም ያጣ አካባበቢ መሆኑ ቀጥሏል፡፡ ለዘለዓለም ወዳጅ ነን ብሎ ሲመፃደቅበት ከነበረው ሻዕቢያም ጋር ግጭቱ ተፋፋመ እንጂ አልበረደም፡፡ ወያኔ በውስጡ በመከፋፈሉም መሰረቴና ጓዳዬ በሚለው በትግራይ ራሱ መንገዳገድ እየመጠባት ነው፡፡ በጥቂቶች ላይ የቆመው የወያኔ ቡድን ይበልጥ እየጠበበ፤ ይበልጥ እየራደ፤ ይበልጥ አፋኝ እየሆነ ወደ ውድቀቱ የፍጥነት ጉዞን ማድረጉ የሚታይ ነው፡፡ ይህን ጉዞ በራሱ ቅራኔ የተነሳ የሚሄድበት ከሆነ ጉዞው ረጅም ሊሆን ይችላል፡፡ ይህን የወያኔ ሁኔታ ተረድቶና ስስ ብልቱን ለይቶ የሚያጠቃ ተቃዋሚ ሀይልና የተደራጀ ሕዝብ ግን ከተነሳ የወያኔ ውድቀት ፈጣንም የማያዳግምም ይሆናል፡፡ ከዚህ ውድቀቱ ሊያድኑት አውቀውም ሆነ ሳያውቁ የሚተባባሩትንም ሕዝብ ሊነቃባቸውና ገለል ሊያደርጋቸው፤ ሊያርቃቸውና ድጋፍ ሊነሳቸው የግድ ያስፈልጋል፡፡ የሕዝብ ጎራ ካልጠራና በፀረ ወያኔው ሰንደቅ ስር ካልተባባረ ድል ዘበት ሊሆን ስለሚችልም ነው፡፡ ወያኔ በየጊዜው ወጥመዱን ሲዘረጋና ሕዝብን ሲከፋፍል፤ የሕዝብን እይታ ወደ አልባሌ አቅጣጫ ሊያዞር ሲነሳ ወገድ ማለትና ትኩረትን ወያኔን ለመጣል በሚካሄደውና መካሄድ መፋፋም ባለበት ትግል ላይ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የወያኔ ቀውስ በቀላሉ የሚወገድ አይደለም፤ ቀውሱን ማባባስና ውድቀቱን ማፋጠን ነው ዋነው ግዳጃችን መሆን ያለበት፡፡

ለወያኔ የማይራራ ቆራጥ ትግል እናካሂድ!!

ወያኔን አስወግደን ሀገራችንን ከጥፋት እናድን!!

ምንጭኝ- ፍኖተ ዲሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ራዲዮ፤



# ማስፈራሪያ ጭራቅ ሆናችሁብ

## ከጌታቸው ኃይሌ

የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር በሚል ስም የሚጠሩት የትግራይ ወያኔዎች ኢትዮጵያን በእጃቸው ጭብጥ በእግራቸው እርግጥ አድርገው ለመግዛት በብዙ ዘዴዎች ተጠቅመዋል:: ዋናው ዘዴያቸው ሰው ከመሆን ወጥተው አውሬ መሆን ነው:: አውሬ ጠላቱ ያደረገውን ሲገድል አይራራም፤ "ይቺ ገና ጨቅላ ግልገል ነች÷ ልማራት፤ ይቺ እመጫት ነች÷ ልተዋት፤ ይኼ አሮጌ ነው÷ ልለፈው" ብሎ አይምርም:: እንዳገኘ በሰላ ጥርሱ ይቦጫጭቀዋል:: የትግሬ ወያኔዎች

እንደዚህ ናቸው:: ለምሳሌ÷ በድርቁ ጊዜ ለተጎዱ ሰዎች በእርዳታ መልክ ከውጪ ሀገር የመጣውን

ገንዘብ ነጥቀው በመውሰዳቸው ከዓሥራ ሶስት ሺ በላይ የሚሆኑ የትግራይ ተወላጆች በረሃብ

እንዳለቁ እራሳቸው እየተናገሩ ነው:: እነዚህን ሰዎች በአውሬ የመሰልኳቸው አምሳያ አጥቼላቸው

ነው እንጂ÷ አውሬ እንደ ወያኔዎች ወገኑን አይበላልም፤ እንደነሱ እናት አይምሬ አይደለም::

ዋናው ዘዴያቸው ወደአውሬነት መለወጥ ሲሆን÷ ሁለተኛው ዘዳያቸው የነማኪያቬሊ ከፋፍለህ

ግዛው ነው:: በሰላም አብሮ የኖረውን ሕዝብ የጎሪጥ እንዲተያይ አድርገውታል:: "ዘርን መናገር

ለነገር" እያልን ለአንድነት ስንል በዘራችን ሲጠሩን መሸማቀቅ ጀምረናል:: አይሆንም፤

አያዋጣምም:: ወያኔዎችን ለማሳፈር ወደዱሮው መመለስ አለብን:: ሁሉም ያለፍርሃት ያለኩራት

ዘሩን መናገር አለበት:: አማራ ነኝ፤ ጉራጌ ነኝ፤ ወላይታ ነኝ ማለት የሚያኮራም ሆነ የሚያሳፍርም

ነገር የለበትም:: ከጎጃም ነኝ፤ ከጎንደር ነኝ፤ ከወለጋ ነኝ ማለት የሚያሳፍርም የሚያኮራም ነገር

የለበትም:: ሁሉም በየዘሩና በያለበት ኢትዮጵያዊ ነው የሚለውን ባፋችን ብቻ ሳይሆን በልባችንም

እናሳድረው::

"ዘር" ማለትን እንወቀው እንጂ አንፍራው፤ በአማርኛ "ዘር" ሁለት ትርጉም አለው፤ አንዱ

ዝምድናን የሚያመለክት ሲሆን ሁለተኛው የተፈጥሮን ልዩነት የሚያመለክት ነው:: አንድ ቤተ ሰብ

ዘሩ ወይ ይጠፋል ወይ ይሰፋና አንድ ሀገር ይሆናል:: ጎሳዎች÷ ነገዶች የሚፈጠሩት በዚህ መንገድ

ነው:: ሁለት ወንድማማቾች ሁለት ዘር ይወጣቸዋል:: ሕዝቦች የተፈጠሩት በዚህ መንገድ ነው::

ካንድ ቤተ ሰብ ወጥተን ጉራጌዎች÷ እንግሊዞች÷ ቅስሮሞዎች÷ ህንዶች÷ ወዘተ ሆነናል:: ይኸ

ስለዝምድና ነው:: የአቶ በቀለ ዘር ነኝ÷ የጉራጌ ዘር ነኝ÷ የቅስሮሞ ዘር ነኝ ማለት በደም

አለመመሳሰልን አያመለክትም:: የሰው ልጅ 99.99 በመቶ ዘሩ አንድ ነው::

በደም አለመመሳሰልን የሚያመለክት የተፈጥሮ ዘር ነው:: በተፈጥሮ የሰው ዘር÷ ያራዊት ዘር÷ የዓሣ

ዘር÷ ያትክልት ዘር ይለያያሉ::

አሁን ይቺን አጭር ጽሑፍ እንድደርስ ወደገፋፋኝ ወደሌላው የትግሬ ወያኔዎች መሠርይ ዘዴ

ልምጣ:: እኛን ሁላችንንም ይመለከታል:: ይኸውም÷ "እንድንገዛችሁ ካልፈለጋችሁ አገሪቷን

ለተገንጣዮች አከፋፍለን እንሄዳለን" የሚሉት ማስፈራሪያ ነው:: በተለይ ማስፈራሪያ ያደረጉት

ቅስሮሞዎችን÷ ቅስጋዴኖችን÷ አፋሮችን÷ ትግራዮችን ነው:: ደቡቦቹንም ሞከር አድርገዋቸው ነበር፤

አልተበገሩላቸውም:: ግን እውነት ቅስሮሞዎች÷ ቅስጋዴኖች÷ አፋሮች÷ ትግራዮች የኢትዮጵያን

አንድነት አይፈልጉም? በእርግጥ የማይፈልጉ ከሆነ÷ አጥጋቢ ምክንያት አላቸው? እውነት

ከተንጣለለ ሰፊ አገር ይልቅ ብጣሽ አገር የሚያስመርጥ ችግር አጋጥሟቸዋል? በአንዲት ኢትዮጵያ

ውስጥ የማይፈታ ብሶት ከየት መጣ? ምንድነው እሱ? በአንድነት ውስጥ የማያገኙት ቢገነጠሉ ግን

የሚያገኙት ጥቅም ምንድን ነው? አማሮቹ÷ ጉራጌዎቹ÷ በጠቅላላው ደቡቦቹ አንድነቱን ሲፈልጉት

ሌሎቹ የማይፈልጉበት ምክንያት ምንድን ነው?

አንድነትን የምትፈልጉ ከሆነ÷ ለምን ማስፈራሪያ ጭራቆች ትሆኑብናላችሁ? ስማችሁ ለምን

የኢትዮጵያን ሕዝብ መጨቆኛ ሲሆን ዝም ብላችሁ ታያላችሁ? ሕዝቡ እኮ በጨቋኞቹ

የሚያማርረውን ያህል እያማረረባችሁ ነው:: በውጭ አገር ከሚኖሩ ትግራዮች ውስጥ ጥቂቶች

ተሰባስበው በወያኔ ከፋፍለህ ግዛ ፖለቲካ እንደማይስማሙ መግለጫ አውጥተዋል:: ለሕሊና ዕረፍት

የሚሰጥ÷ እነሱንም ከኀላፊነት የሚያድን እርምጃ ነው::

ወያኔዎች ማስፈራሪያ ጭራቅ ለአደረጓቸው ኢትዮጵያውያን የማቀርበው ሐሳብ እነዚህ የትግራይ

ልጆች የወሰዱትን እርምጃ እንዲወስዱ ነው:: ሲሆን ሁሉም በመሪዎቻቸው አማካይነት አንድ ቦታ

ተሰባስበው÷ ካልሆነም በየድርጅታቸው ሆነው በኢትዮጵያ አንድነት የሚያምኑ መሆናቸውን

መግለጫ በማውጣት መለስንና አጃቢዎቹን እንዲያሳፍሩት አሳብ ላቅርብ:: ከመለስ የተለያችሁ

መሆናችሁን ሕዝብ የሚያውቅላችሁ ይኸን ዓይነት መግለጫ ስታወጡ ነው::

እንዲህ ያለ መግለጫ ለማውጣት ጊዜው አመቺ ሆኗል:: ምክንያቱም መገንጠልን የሚፈቅደውን

የሕገ መንግሥት አንቀጽ ከደገፉት ውስጥ ብዙዎቹ አሁን ጉዳቱን እያዩ ተጸጽተዋል:: በብሔር

(በዘር) የተደራጁ ፓርቲዎችም በኢትዮጵያ አንድነት እንደሚያምኑ በይፋ ባደባባይ ሲናገሩ

ተሰምተዋል:: አሁን የቀራቸው ይኸንኑ አቋማቸውን በመግለጫ መልክ ለኢትዮጵያና ለዓለም ሕዝብ

ማሳወቅ ነው:: የብሔር (የዘር) ድርጅቶች ይኸንን ቢያደርጉ መግለጫው የወጣ ዕለት የሀገሪቷ መዳን

ይረጋገጣል፤ ሕዝቡም ከሥጋት ተላቅቆ በሰላም ያድራል:: ወገኖቹ ያደርጋችኋል:: አንቀጽ 39

የመለስና የጓደኞቹ ጥርስ የሌለው ተናካሽ ውሻ÷ የማይፈሩት ማስፈራሪያ ሆኖ ይቀራል:: እርቅ

ይወርዳል፤ ጅርጅቶች ባገር ከፋፋይ ጠላት ላይ አብረው ይቆማሉ:: ወያኔን መቃወማቸው ካልቀረ

ይኸንን አቋም በመግለጫ መልክ ማውጣት አንዱ የትግል ስልት ይሆናል::

# በአንድ ስብሰባ ላይ መገኘት መደገፍ ወይም አለመደገፍ ማለት አይደለም

የሀገራችን ሁኔታ በሚመለከት በርካታ እጅግ ብዙ ስብሰባዎች በተለያዩ ግለሰቦችና ድርጅቶች ሲካሄዱ ቆይተዋል። በግለሰብም ሆነ በድርጅቶች የሚጠሩት ስብሰባዎች ዓላማቸው ምንም ይሁን ምንም የሀገርን ጉዳይ የሚመለከት አጀንዳ ይዘው ነው የሚነሱት። ነገር ግን ለሚያቀርቡት ጥሪ ምላሹ በጣም ዝቅተኛ ስለሆነ ተስፍ አየሚያስቆርጥ ሆኖ በመገኘቱየሀገርን ጉዳይ በሚመለከት ተመሳሳይ ስብሰባ ለማዘጋጀት ግለሰብም ሆነ ድርጅት ብዙም የሚደፍር የለም። አንድ ድርጅት ወይም ግለሰብ በሚጠራው ስብሰባ ላይ መገኘት ያንን ድርጅት ወይም ግለሰብ መደገፍ ማለት አእይደለም። የሀገር ጉዳይ ነውና መደገፍ ካለበት መደገፍ፣ መደገ ከሌለ በትም መቃወም ስለሚቻል የግድ የደጋፊዎች ስብሰባ ብቻ መሆን የለበትም።፡ተቃዋሚም ሆኖ የማይስማሙበትን ነገር በአካል ተገኝቶ ሃሳብን መግለጽ ይቻላል።

በምንደግፈው ድርጅት ስብሰባ ላይ ተገኝተን መስማት የምንፈልገውን ብቻ ሰምተን የምንወጣ ከሆነ የሚገኘው መረጃ ስለምንደግፈው ድርጅት እውነተኛ አቁዋም የሚኖረን ግንዛቤ በጣም ውሱን ይሆናል።፡በተለይም በአብዛኛዎቻችን ድርጅታችን ብቻ ስለሆነ የሚሰማንን ደፍረን የመናገርና አስተያየት መስጠት የተለማመድነው ባለመሆኑ ለድርጅቶች የአመራር አካላት የመሰላቸውን ለማድረግ እንዲችሉ እድል እየሰጠናቸው ነው። በአንጻሩም አንዳንዳችን በማንደግፈው ድርጅት ላይ እንኩዋን ብንገኝም ጥሩ ጎኑን ወደጎን በመተው ስህተት መስሎ በታየን ላይ ብቻ በማተኮር እንዲያውም ድርጅቶችንና ግለሰቦችን በማያያዝ የግለሰቦችን የቀድሞ ታሪክ በማንሳት ድርጅቶች እንዳያድጉ ስናደርግ መቆየታችን በተደጋጋሚ ያየነው ሃቅ ነው።፡በእርግጥ፡የድርጅት መሪዎችን ያለፈ ታሪክ ጠቃሚ ቢሆንም የሚያራምዱትን ድርጅት ዓላማና አሠራር በመከታተል የሚመስለንን አስተያየት ከድርጅቱ መመሪያና ደንብ ተነስተን ለግምገማ ያመቻል። ሀገራችን የሁላችንም ናት። ቀደም ሲልም ሆነ አእሁን ሀገራችን ያለችበትን ሁኔታ የማሳወቁ፣ በሕዝቦችዋ ፍትህና ነጻነት ማጣት. መራብና መራቆት፣ እሥራትና ሞት እንግልት በስብሰባም ሆነ በሰላማዊ ሰልፍ ብሶታቸውን ሲገልጹ የቆዩ ኢትዮጵያዊያን ቁጥር በቶሮንቶ ውስጥ ካለው ኢትዮጵያዊያኖች ጋር ሲነጻጸር ቁጥሩ በጣም የሚያሳፍር ነው።፡ሀገር ቤት ውስጥ ያሉት ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች ተቁዋቁመው የህይወት መስዋእትነት እየከፈሉ ባሉበት ጊዜ እኛ ድጋፋችንን ተቀራርበን በመወያየት እንዴት መርዳት እንዳለብን እንኩዋን ለመነጋገር አለመሞከራችን የሚያሳዝን ነው።

እስቲ ወደ ህሊናችን ተመልሰን ራሳችንን እንጠይቅ፤ ለዚህ ሕዝብ ምን አድርጊያለሁ? ማድረግ የምችለውስ ምንድን ነው? የሚሉትንን አየመሳሰሉትን ጥያቄዎች አንስተን መልስ ለመስጠት ከሞከርን አንድ አቁዋም ላይ እንድንደርስ ያደርገናል።፡እንደ አንድ ዜጋ የዜግነት ድርሻችንን መወጣት አለብን።፡ይህንንም ለማድረግ ብዙ አማራጮች ስላሉ ሌላው ቢቀር ከሕሊና ወቀስ አለመዳን እንሞክር።

በዚህ አጋጣሚ ያሉትም ድርጅቶች ቢሆኑ ከዚህ በፊት በነበሩት ሁኔታዎች ተስፍ አባለመቁረጥ ስለድርጅቶቻቸው ቢያንስ በሁለትና ሶስት ወር እንዳመችነቱ ስለሀገራችን ሁኔታ፣ ስለድርጅታቸውና እዚህ ካለነው ኢትዮጵያዊያን የሚጠበቅብንን ባለመሰልቸት ቢገልጹልን ሁኔታዎች ሊቀየሩ ይችላሉ። ከቁጭትና ከንፈር መምጠጥ የዘለለ ሥራ ከሁላችንም ስለሚጠበቅ ድርጅቶች ከአባሎቻቸው ውጭ ከሚያደርጉት ስብሰባ በተላያዩ ጉዳዮች ላይ የተለያዩ ምሁራንን እየጋበዙ ቢያወያዩን ብዙዎቹ ጉዳዮች ሊያቀራርቡንና ወደ አንድ ስብስብ ሊያመጡት ስለሚችል ድርጅቶች ተንቀሳቀሱ። በክልላችሁ ብቻ ተወስናችሁ የምታደርጉት እንቅስቃሴ ብዙም አያስኬድምና አሠራራችሁን ፈትሹት።፡

ይህ ጉዳይ በድርጅቶች ላይ የሚተው ጉዳይ ባለመሆኑ ጠቅላላ ህብረተሰቡን የሚመለከት ስለሆነ ከድርጅቶች ውጭ የሆኑ ምሁራንም ቢሆን የውይይት መድረክ በማዘጋጀት ሁሉንም የሚያሳትፍ ዝግጅት ብታዘጋጁልን ከሚጠበቅባችሁ የዜግነት ድርሻ አንዱን እንደተወጣችሁ የሚቆጥር ነውና እባካችሁ እውቀታችሁን አካፍሉን እንላለን።

ስለዚህ እባካችሁ በሀገራችን ጉዳይ ላይ ግንባር ቀደሞች እንሁን፤ የሚሰማንን ተገናኝተኔእንወያይ። እንደዜጋ የዜግነታችንን እንወጣ።፡እንደሰውም ለቀሩት ሀገር ቤት ላሉት ወገኖቻችን እናስብላቸው። ራሳችንን በነሱ ቦታ አስቀምጠን እንንየው። ለነጻነትና ለፍትህ የሚደረግ ትግል ድንበርና ርቀት አይወስነውምና ባለንበት ሆነን ለሀገራችን ህልውና እንታገል።

ደረጀ (ከቶሮንቶ)




# Looking forward to going back?

## Lufthansa announces extended service to Addis Ababa with additional connections on Ethiopian Airlines



This summer, Lufthansa makes it easier to share the rich history and colorful traditions of Ethiopia with the people you love: 13 months of sunshine, the sound of drumbeats announcing an afternoon service, the aroma of coffee beans roasted as you wait, and gathering with family to tear the injera and dip it in your favorite sauces.

Lufthansa announces extended service to Addis Ababa with additional connections on Ethiopian Airlines. To get there in comfort, we provide daily service from Toronto to our hub in Frankfurt, where quick, seamless connections to Bole International Airport (ADD) are available ten times per week, some made possible through our partner, Ethiopian Airlines.

**Like you, we have roots in Africa**

To offer this expanded timetable, we've partnered with Ethiopian Airlines, the flag carrier of Ethiopia. Ethiopian Airlines has grown to become one of the continent's leading carriers.

Lufthansa is proud of its forty-year history of service in Ethiopia and is very pleased that an increased demand has allowed for an expanded flight schedule.

The route will be served by an Airbus A340-300, offering exemplary service and excellent entertainment on personal video screens in all three classes. Choose from a wide selection of current films, audio books or music at the touch of a button, right from your fingertips.

Visit **lufthansa.com** now to book your journey back to Ethiopia!

There's no better way to fly.℠

Lufthansa